# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁ. 231028

ሐምሌ 19 ቀን 2015 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. ብርሃኑ አመነዉ

2. ረታ ቶሎሳ

3. በዕዉቀት በላይ

4. ቀነዓ ቂጣታ

5. ኑረዲን ከድር

አመልካች...... አቶ ከተማ ተዘራ

ተጠሪ............ ቫዮሌት ጠቅላላ የንግድ ሥራ ድርጅት ኃ/የተ/የግ/ማህበር

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሥራ ስንብት ክርክር የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን በሱሉልታ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ይህ ጉዳይ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ አመልካች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.394056 በ25/08/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሽ በሥር ፍ/ቤት ባቀረበዉ ክስ ከሳሽ በተከሳሽ ድርጅት በ26/2/2008 ዓ.ም የምርት ቡድን ተቆጣጣሪ የሥራ መደብ ላይ በወር ደመወዝ ብር 6090 ተቀጥሬ እየሰራሁ የቆየሁ ሲሆን፣ ድርጅቱ በእኔ ሥር የሚሰሩት ሰራተኞች አምስት በ21/1/2014 ዓ.ም ሥራ እንዲገቡ ማስታወቂያ ያወጠ ቢሆንም ሠራተኞቹ በራሳቸዉ ማስታወቂያዉን እንደማይቀበሉ ገለጸዉ በተጠቀሰዉ ቀን ከሥራ የቀሩ ሆኖ ሳለ እነዚህ ሰራተኞች ከሥራ የቀሩት እኔን የማይመለከተኝ ሆኖ እያለ፣ ሰራተኞቹን ከሥራ እንዲቀሩ አድርገአል በሚል ምክንያት በ4/2/2014 ዓ.ም ከሕግ ዉጭ

ከሥራ ያሰናበተኝ ስለሆነ ፣ ስንብቱ ሕገወጥ ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሰረት ተገቢ ክፍያዎች እንዲከፈሉኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተከሳሽ በዚህ ክስ ላይ ባቀረበዉ መልስ ከሳሽ በተከሳሽ ድርጅት ዉስጥ በምርት ቁጥጥር የሥራ መደብ ላይ ተቀጥሮ የሚሰራ ሲሆን የቡድን ሀ በመሆን እየሰራ እያለ የዚህ ቡድን ሰራተኞች በ21/1/2014 ዓ.ም ከ8፡30 ሰዓት ጀምሮ ሥራ መግባት ሲገባቸዉ ሳይገቡ በመቅረታቸዉ፣ የድርጅቱ መልካም ስም ላይ ጥቁር ነጥብ የጣለና የድርጅቱ ገቢ እንዲወርድ ያደረገ መሆኑን ተከትሎ፣ ድርጅቱ ጉዳዩን ሲያጣራ ሰራተኞች ሥራ እንዳይገቡ በመሓላ በማስገደድ በመፎከር በማስፈራራት ሥራ እንዳይገቡና እንዲቀሩ ያደረጋቸዉ ከሳሽ መሆኑን የሰራተኛ ማህበር እና የወረዳዉ ሰራተኛ ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት አረጋግጦታል፡፡ ከሳሽ ሰራተኞች ሥራ እንዳይገቡ ከልክሏቸዉ ለራሱ ግን ወደ ሥራ በመምጣቱ በዚህ ምክንያት በድርጅቱ ላይ ጉዳት ደርሷል፡፡ በመሆኑም ተከሳሽ ከሳሽ በፈጸመዉ ጥፋት ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ዉሉን በማቋረጥ ያሰናበት ስለሆነ ስንብቱ ሕጋዊ ነዉ፤ ከሳሽ እንዲከፈለዉ የጠየቃቸዉ ክፍያዎች ልከፈሉት አይገባዉም ተብሎ ክሱ ዉድቅ እንዲደረግልን በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የወረዳዉ ፍ/ቤት የሰዉ ምስክሮችን በመስማትና የሰነድ ማስረጃን በመመርመር ባሳለፈዉ ዉሳኔ ከሳሽ በተከሳሽ ድርጅት የምርት ቁጥጥር ሰራተኛ ሆኖ የቡድን ሀ ሰራተኞች በ21/1/2014 ዓ.ም በድርጅቱ ላይ ሰራተኞች እንዲነሳሱ በማድራጀት ሥራ እንዳይገቡና ሥራ ከገቡ እርምጃ እንደሚወስድባቸዉ የተለያዩ ዛቻ በመፈጸም ሰራተኞቹ ሥራ እንዳይገቡ በማድረግ ለራሱ የሥራ ሰዓት አክብሮ እንደገባ በማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ፣ በዚህ ምክንያት በድርጅቱ ላይ ጉዳት የደረሰ በመሆኑ፣ ይህ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27 (ሐ) እና (ሸ) መሰረት ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ የሚያሰናብተዉ በመሆኑ፣ የሥራ ስንብቱ ሕጋዊ ነዉ፤ ከሳሽ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት የጠየቀዉ ክፍያ ሊከፈለዉ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

የሥር ከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የሰበር አቤቱታ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቶቹ ቅሬታዉን ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ12/11/2014 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ አመልካች የተጠሪ ድርጅት የቡድን ‹‹ሀ›› ሥራ መሪ ቢሆንም በእኔ ሥር የሚታዘዙትን ሰራተኞች በ21/1/2014 ዓ.ም ሥራ እንዳይገቡ አላስተባበርኩም፣ አላስፈራረሁም፣ አልከለከልኳቸዉም እንጂ የተጠሪ ሰራተኞች ከግላቸዉ ከሥራ በመቅረታቸዉ በተጠሪ ድርጅት የምርት ሥራ መስተጓጎል፣ የድርጅቱ የመልካም የንግድ ስም መቀነስና ለተፈጠረዉ ሁከት ኃላፊነት የለብኝም፡፡ በራሳቸዉ ጊዜ ሥራ ላይ ያልተገኙ ሰራተኞች ራሳቸዉን ለማዳን ሲሉ በአመልካች ላይ በአመካኙት ምክንያት አመልካችን ከሥራ ማሰናበት ከሕግ ዉጭ ነዉ፡፡ አመልካች ያቀረብኳቸዉ የሰዉ ምስክሮች ሰራተኞቹ በራሳቸዉ ከሥራ ማቅረታቸዉ እንጂ በአመልካች ተጽዕኖ አሳዳሪነት እንዳልሆነ በበቂ ሁኔታ ያረጋገጡ ሆኖ ሳለ፣ የተጠሪ ምስክሮችን ግን የሰሚ ሰሚ እንጂ ከሥራ የሚያሰናብተኝ ምክንያት መኖሩን ባላረጋገጡበት የሥር ፍ/ቤቶች የሥራ ስንብቱ ሕጋዊ ነዉ በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት

ስለሆነ እንዲሻርልኝ አመልካች ወደ ሥራው ሊመለስ ይገባል ተብሎ እንዲወሰንልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣አመልካች በዕለቱ የሥራ ሰዓት አክብሮ በሥራው ተገኝቶ እያለ ስለሌሎች ሰራተኞች መቅረት ምክንያት ሆነአል በሚል ስንብቱ ሕጋዊ ነው የተባለበትን አግባብነት ከአዋጁ አንቀጽ 27 (ሐ) (ሸ) አንጻር ለመመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘው መሰረት ታህሳስ 19 ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት ባጭሩ፡ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች የአሁን ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተው በፈጸመው ጥፋት መሆኑን በማረጋገጥ የአመልካች የሥራ ዉል የተቋረጠው በሕጋዊ መንገድ ስለሆነ የአመልካች አቤቱታ ዉድቅ ሆኖ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲጸናልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ አመልካች በ3/5/2015 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነው አመልካች ባቀረበው ክርክር አመልካች በተጠሪ ድርጅት የምርት ቁጥጥር የሥራ መደብ ተቀጥሬ እየሰራሁኝ በእኔ ሥር የሚታዘዙትን የቡድን ‹‹ሀ›› ሰራተኞች በ21/1/2014 ዓ.ም ሥራ እንዳይገቡ በዛቻና በማስፈራራት የከለከልኩኝ ሳይኖር፣ ሰራተኞቹ በራሳቸው ሥራ አንገባም በማለት ገልጸው ቀርተው እያሉ፣ እኔ በእለቱ ስራ ገብቼ እያለሁኝ፣ የሌሎች ሰራተኞችን ጥፋት በማመካኘት ተጠሪ ከሕግ ዉጭ ከሥራ አሰናብተኝ እያለ የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካች የሥራ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት የአመልካችን ክስ ዉድቅ ያደረጉት ከሕግ ዉጭ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ባቀረበው ክርክር አመልካች የቡድን ‹‹ሀ›› ሰራተኞችን በመሐላ በማስገደድ በዛቻ በማስፈራራት በ21/1/2014 ዓ.ም ሥራ እንዳይገቡ በማድረግ የተጠሪ ድርጅት ገቢ እንዲያጣና ጉዳት እንዲደርስበት ያደረገው በመሆኑ ያለማስጠንቀቂያ በሕግ አግባብ ከሥራ የተሰናበተ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ አንጻር የሥር ፍ/ቤት በማስረጃ ከረጋገጠው ፍሬ ነገር መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካች በተጠሪ ድርጅት የምርት ቁጥጥር ሰራተኛ ሆኖ የቡድን ‹‹ሀ›› ሰራተኞች በ21/1/2014 ዓ.ም በድርጅቱ ላይ እንዲነሳሱ በማድራጀት ሥራ እንዳይገቡና ሥራ ከገቡ እርምጃ እንደሚወስድባቸው በዛቻ ማስፈራራትን ሰራተኞቹ ሥራ እንዳይገቡ በማድረግ ለራሱ የሥራ በመግባት፣ በተጠሪ ድርጅት ላይ ገቢ የማጣት ጉዳት ያደረሰ መሆኑን በሰዉና በሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው አመልካች የቡድን ሰራተኞች ሥራ እንደገቡ ከከለከላቸው በኋላ እርሱ ጉዳይ ምንም ዓይነት ግንኙነት እንደሌለዉና ነጻ መሆኑን በማስመሰል የሥራ ቦታ የተገኘ መሆኑን እና ሰራተኞች ሥራ እንዳይገቡ በማድረጉ የተጠሪ ገቢ እንዲያጣ በማድረግ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ የተረጋገጠ ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27 (1) (ሐ) (ሸ) በመተላለፍ ሕገወጥ ድርጊት የፈጸመ በመሆኑ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ የሚያሰናብተው ጉዳይ ነዉ፡፡ በመሆኑም የአሁን ተጠሪ አመልካች በሥራ ላይ በፈጸመው ጥፋት ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ማሰናበቱ በሕግ አግባብ ነው ከማለት ባለፈው ሕገወጥ የሥራ ስንብት ነው የሚያስብል ምክንያት የለም፡፡ አመልካች ያቀረበው ቅሬታ የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ጉዳይ በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80 (3) (ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር

1234/2013 አንቀጽ 2 (4) (ለ) እና 10 (1) (መ) መሰረት የአመልካች ቅሬታ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን የሚያመለክት ስላልሆነ ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪ የአመልካችን የሥራ ዉል በማቋረጥ ከሥራ ያሰናበዉ በሕግ አግባብ ስለሆነ አመልካች እንዲከፈለዉ የጠየቀዉ ክፍያዎች ተቀባይነት የለዉም በማለት አመልካችን ክስ ዉድቅ በማድረግ ያሳለፉት ዉሳኔ በሕግ አግባብ የተሰጠ ነዉ ከማለት ባለፈ የሚነቀፍበት የህግ አግባብ ባለመኖሩ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.394056 በ25/08/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
3. ግራ ቀኝ የሰበር ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/በ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም